`የሰ/መ/ቁ. 154450

ሀምሌ 30 ቀን 2010 ዓ.ም.

ዳኞች - ዳኜ መላኩ

ተኽሊት ይመስል

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

ተሾመ ሽፈራው

አብዬ ካሳሁን

አመልካች - አቶ አላምር አድማሴ ቀረቡ

ተጠሪዎች - 1ኛ. ወ/ሮ ውብአለች ጸጋው

2ኛ. አቶ ሀይሌ ይታይህ

መዝገቡን መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍ ር ድ

ለሰበር ክርክሩ መነሻ የሆነው የአሁን አመልካች በአማራ ክልል ምዕራብ ጎጃም ዞን በደጋ ዳሞት ወረዳ ፍርድ ቤት የአሁን ተጠሪዎች ሲከራከሩበት በነበረው የባልና ሚስት ንብረት አከፋፈል የአፈፃፀም ጉዳይ ላይ ያቀረቡት አቤቱታ ነው፡፡

አመልካች ያቀረቡት አቤቱታ ይዘት ባጭሩ፡- ከ2ኛ ተጠሪ ጋር ክርክር አድርገን በዕርቅ ውል የለቀቀልኝን በፈረስ ቤት ከተማ ሰፈር 4 ከተባለው ቦታ የሚገኝ አዋሳኙ በምስራቅ አቶ ደምስ አስረስ፣ በምዕራብ አያሌው ካሳ፣ በሰሜን መንገድ፣ በደቡብ መንገድ የሆነ 250 ካሬ ሜትር ቦታ እና 66 ቆርቆሮ ቤት ተጠሪዎች በባልና ሚስት ሃብትነት የአፈፃፀም ክርክር እየተደረገበት ለማስረከብ በቀጠሮ ላይ የሚገኙ በመሆኑ አፈፃፀሙ ከመቀጠሉ በፊት በቤቱና ቦታው ላይ ያለኝ የቀዳሚነት መብት ይረጋገጥልኝ በማለት ዳኝነት መጠየቃቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

1ኛ ተጠሪ በሰጡት መልስ ክርክር በተነሳበት ቤትና ቦታ ላይ ባለቤቴ (2ኛ ተጠሪ) እና አመልካቹ ታርቀው መስማማታቸውን አላውቅም፤ እኔ ያልታረቅሁበትና ያልተስማማሁበት በመሆኑና መብቴንም የሚነካ በመሆኑ ስምምነታቸው ተቀባይነት የለውም፤ በንብረቱ ተከራክሬ የባልና ሚስት የጋራ መሆኑ የተወሰነልኝ በመሆኑ አቤቱታው ውድቅ ይደረግልኝ በማለት ተከራክረዋል፡፡ 2ኛ ተጠሪ በበኩላቸው ከአመልካች ጋር በዚህ ቦታ እና ቤት መታረቃችን ባይካድም የታረቅሁት በራሴ ድርሻ እንጂ በ1ኛ ተጠሪ ድርሻ አይደለም ብለዋል፡፡

ጉዳዩ በዚህ መልኩ የቀረበለት የወረዳው ፍርድ ቤት ክርክርና ማስረጃውን መርምሮ ምንም እንኳ ክርክር ያስነሳው ቤት በ2ኛ ተጠሪ ስም ተመዝግቦ እንደሚገኝ የከተማው መሪ ማዘጋጃ ቤት ቢገልጽም አመልካችና 2ኛ ተጠሪ በመ/ቁ 10344 በነበራቸው ክርክር አመልካች ብር 25000.00 (ሃያ አምስት ሺህ) ለ2ኛ ተጠሪ በመክፈልና 2ኛ ተጠሪም ቤቱን ለመልቀቅ የተስማሙ በመሆኑ፤ ያደረጉት ስምምነትም በሙሉው ቤት ላይ ስለመሆኑ አመልካች ባቀረቧቸው ምስክሮች የተረጋገጠ በመሆኑና ስምምነታቸውም ለፍርድ ቤቱ ቀርቦ ፀድቆ የሚገኝ በመሆኑ አከራካሪው ቤት የአመልካች ነው ለተጠሪዎች የባልና ሚስት ሃብት ክፍፍል አፈፃፀም ሊውል አይገባም በማለት ወስኗል።

በዚህ ውሳኔ ላይ የአሁን 1ኛ ተጠሪ የይግባኝ ቅሬታቸውን ለምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት ያቀረቡ ሲሆን ፍርድ ቤቱ የይግባኝ ክርክሩን ሰምቶ በሰጠው ውሳኔ ቤቱ የተጠሪዎች (የባልና ሚስት) የጋራ ሃብት ነው ተብሎ የተወሰነ ሲሆን አፈፃፀሙም በዚህ ውሳኔ አግባብ የቀጠለ መሆኑን መዝገቡ ያስረዳል፤ ባልና ሚስቱ ተከራክረው ቤቱ የጋራ ነው ተብሎ ውሳኔ ያረፈው በቀን 14/06/2008 ዓ.ም ነው፤ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የታረቁት ደግሞ በቀን 30/06/2008 ዓ.ም መሆኑን ከውሳኔው ግልባጭ መረዳት ይቻላል፤ ይህ የሚያሳየው በባልና ሚስቱ ክርክር ቤቱ የጋራ ነው ተብሎ አስቀድሞ ከተወሰነ በኋላ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ የዕርቅ ስምምነት ያደረጉ መሆኑን ነው፤ ስለሆነም የሥር ፍርድ በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገ የእርቅ ውል መኖሩን በማረጋገጥ ብቻ 1ኛ ተጠሪ ከባለቤቷ ጋር ተከራክራ የጋራ መሆኑ ተረጋግጦ የተወሰነላትን ቤትና ቦታ ለቀሽ አስረክቢ ማለቱ በአግባቡ አይደለም በማለት የስር ፍርድ ቤት ያሳለፈውን ውሳኔ አሻሽሎ የአከራካሪው ቤትና ይዞታ ግማሽ የ1ኛ ተጠሪ ነው ፣ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በፈፀሙት የእርቅ ውል መሰረት ግማሹ የቤትና ይዞታ ድርሻ ለአመልካች ይገባል በማለት ወስኗል።

አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚና ሰበር ችሎቶች ቅሬታቸውን ቢያቀርቡም ተቀባይነት አላገኙም። የሰበር አቤቱታው ለዚህ ፍርድ ቤት የቀረበው ይህን በመቃወም ነው። አመልካች የካቲት 21/2010 ዓ.ም ያቀረቡት የሰበር ማመልከቻ በአጠሪ ችሎቱ ተመርምሮ ጉዳዩ ለሰበር ችሎት እንዲቀርብ እና ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጓል። በዚህ መሰረት አመልካችና 1ኛ ተጠሪ የስር ክርክራቸውን በማጠናከር በጽሁፍ የተለዋወጡ ሲሆን 2ኛ ተጠሪ መጥሪያ ደርሷቸው መልስ ስላላቀረቡ መልስ የመስጠት መብታቸው ታልፏል።

ከፍሲል ባጭሩ የገለጽነው የጉዳዩን አመጣጥ ሲሆን በበኩላችን ቅሬታ በቀረበበት ውሳኔ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ ስህተት መኖር አለመኖሩን መርምረናል። እንደመረመርነው በአከራካሪው ቤት ላይ አመልካችና 2ኛ ተጠሪ የዕርቅ ስምምነት ማድረጋቸውና በሌላ በኩል ደግሞ ባልና ሚስቱ ተከራክረው ቤቱ የጋራ ነው ተብሎ ውሳኔ አርፎበት በአፈፃፀም ላይ ይገኝ እንደነበር ግራቀኙን አላከራከረም። ንብረቱ የባልና ሚስት የጋራ ሃብት ነው ተብሎ ውሳኔ ያረፈው በ14/06/2008 ዓ.ም መሆኑና አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር የታረቁት ደግሞ በቀን 30/06/2008 ዓ.ም

መሆኑም ፍሬ ነገር ባጣራው ይግባኝ ሰሚ ችሎት ተረጋግጧል። ስለሆነም አከራካሪው ቤትና ይዞታ የተጠሪዎች የጋራ ሃብት ነው ተብሎ 1ኛ ተጠሪ ግማሽ ድርሻ እንዳላቸው በፍርድ ውሳኔ ከተረጋገጠ በኋላ የዕርቅ ስምምነቱ በአመልካችና 2ኛ ተጠሪ መካከል የተደረገ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። በዚህ ሁኔታ ደግሞ 2ኛ ተጠሪ በባልና ሚስት ክርክሩ ፍርድ ያረፈበትን ጉዳይ ዋጋ በሚያሳጣ መልኩ ከድርሻቸው በላይ በሙሉ ቤቱ ላይ የዕርቅ ስምምነት ለማድረግ የሚያስችል መብት የሌላቸው ሲሆን የተደረገው ስምምነትም በድርሻቸው ላይ ሊፈፀም ከሚችል በቀር የ1ኛ ተጠሪን ድርሻ የሚነካ ሊሆን አይችልም።

በአጠቃላይ ይግባኝ ሰሚው የዞኑ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የአከራካሪው ቤትና ይዞታ ግማሹ የ1ኛ ተጠሪ ነው፣ አመልካች ከ2ኛ ተጠሪ ጋር በፈፀሙት የእርቅ ውል መሰረት ግማሹ የቤትና ይዞታ ድርሻ ለአመልካች ይገባል በማለት መወሰኑና ይኸው ውሳኔ በበላይ ፍርድ ቤቶች ተቀባይነት ማግኘቱ ህጉን የተከተለ ነው ከሚባል በቀር በውሳኔው መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሟል የሚሰኝ ባለመሆኑ ተከታዩን ወስነናል።

<u>ው ሳ ኔ</u>

1. የምዕራብ ጎጃም ዞን ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 69114 ግንቦት 4/2009 ዓ.ም ያሳለፈው ውሳኔ እንዲሁም የአማራ ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 01-46046 በ21/10/2009 ዓ.ም እና የክልሉ ሰበር ችሎትም በመ/ቁ 03-68952 በ21/05/2010 ዓ.ም ያሳለፋት ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 348(1) መሰረት ጸንቷል።
2. የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል።
3. በዚህ ችሎት ፊት ስለተደረገው ክርክር ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ።

መዝገቡ ተዘግቷል ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፋ/ዘ